**ሴፕተምበር 17 2013 QuickNotes የዜና መፅሄት**

**የማህበረሰብ ቀኖች ከበላይ ተቆጣጣሪ Starr (ስታር) ጋር**

የበላይ ተቆጣጣሪ Joshua Starr (ጆሹዋ ስታር) ትም/ቤቶች የሚጎበኙበት፣ ከመምህራን ጋር የሚገናኙበትና ከወላጆችና ከማህበረሰብ አባላት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች የሚመልስበት አራት የማህበረሰብ ቀኖች ይኖሩታል። እያንዳንዱ የማህበረሰብ ቀን፣ ህዝቡ ጥያቄ የሚያቀርብበትና ሃሳቦችና ፅንሰሀሳቦች በሚጋራበት በTown Hall (የከተማ አዳራሽ) ክውነት በ7:30 p.m. ያበቃል።

የመጀመርያው የማህበረሰብ ቀን የተመደበው ለሰኞ ኦክቶበር 14 ነው፣ የሚያካትታቸውም ትም/ቤቶች ክላርስበርግ፣ ፑልስቪል፣ ዳማስከስ፣ ጌተርስበርግ፣ ሴኔካ ቫሌ፣ ዋትኪንስ ሚል፣ ኖርዝዌስት እና ኲዊንስ ኦርቻርድ መንደሮች የሚገኙትን ነው። የከተማ አዳራሽ ስብሰባ በክላርስበርግ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት በ7:30 p.m. ይጀምራል።

በከተማ አዳራሽ ስብሰባ ወቅት ነፃ የህፃናት እንክብካቤ እና የትርጉም አገልግሎቶች ይኖራሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ [Superintendent's page (የበላይ ተቆጣጣሪ ገፅ)] ይጎብኙ ወይም 301-279-3100 ይደውሉ።

*የተማሪ የከተማ አዳራሾች*

Dr. Starr (ዶ/ር ስታር) ስድስት የተማሪ የከተማ አዳራሽ ስብሰባዎችም ያካሂዳል—ሶስት በ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች እና ሶስት በመካከለኛ ደረጃ ትም/ቤቶች። የመጀመርያው የከተማ አዳራሽ ስብሰባ በፑልስቪል 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ሀሙስ ኦክቶበር 17 ይከናወናል።

በከተማ አዳራሽ ስብሰባዎች Dr. Starr (ዶ/ር ስታር)ን በጣም ስለሚያስፈልጓቸው ጉዳዮች ከተማሪዎች በቀጥታ ለመስማት ያስችላቸዋል። የተማሪ የከተማ አዳራሾችን የሚያስተናግደው Justin Kim (ጁስቲን ኪም)፣ በትምህርት ቦርድ የተማሪ አባል ነው። የከተማ አዳራሾች በMCPS ድር ይመዘገባሉ እናም በMCPS ቴሌቪዥን ይታያሉ።

**የተማሪ የከተማ አዳራሾች**

**ነፃ የቤት ስራ እርዳታ እዚህ ይገኛል!**

**የቤት ስራ ቀጥታ** Live (**ህያው አቅርቦት**)! **ለ**28**ኛው ወራት ተመልሷል፣ ከ**K – 12**ኛ ክፍሎች ለሚገኙ ተማሪዎች ከ**MCPS **መምህራን ነፃ እገዛ እያቀረበ። ተማሪዎች የ**HHL (**የቤት ስራ** Live) **መምህራንን በቴሌፎን ከ**4–6 p.m. **በኢንተርኔት መስመር ላይ ደግሞ ከ**4–9 p.m. **ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ሮብ እና ሀሙስ ማግኘት ይችላሉ።**

**ተማሪዎች** HHL**ን ለማግኘት በርካታ መንገዶች አሏቸው። ጥያቄዎች በነዚህ በኩል ማቅረብ ይችላሉ፦**-

- **የቴሌፎን ጥሪ በ**301-279-3234 **በማድረግ**
- **የ**HHL**ን ድር ጣብያ በመጎብኘት** (AskHHL.org)
- **የቴክስት መልእክት ወደ** 724-427-5445 **በመላክ**
- **ኢሜይል በመላክ** (question@AskHHL.org)
- **በፌስቡክ** (Facebook) **መልእክት በመለጠፍ** (facebook.com/AskHHL)

HHL **ለቴክስት፣ ኢሜይልና ፌስቡክ ከ**4–9 p.m. **መልስ ይሰጣል። በቴሌቪዥን** live **መልስ የሚሰጡባቸው ቀኖች ማክሰኞ፣ ሮብና ሀሙስ ናቸው። በሌላ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በቴክስት ወይም በኢሜይል መልስ ያገኛሉ።**

HHL **በቴሌቪዥን** MCPS-TV (Comcast 34, Verizon 36, RCN 89) **ማየት ይቻላል እናም በ**MCPS **ድር ጣብያ።**

[**የ**HHL **ድር ጣብያ**]

**የቤት ስራ፡ ወላጆች እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ**

**የቤት ስራ ተማሪዎች በመማርያ ክፍል የተማሩትን ልምምድ ለማድረግና የተማሩትን ፍሬነገር ቁጥጥራቸው ስር ለማዋል የሚያስችል ታላቅ እድል ነው። ለወላጆችም በልጆቻቸው ትምህርት ለመሳተፍ ተጨማሪ እድል ነው። ልጆችን በቤትስራ ማገዝ ሁልግዜ ቀላል አይደለም ለተማሪዎችም ትርጉም እንዲኖረው በአስተማሪዎች፣ ተማሪዎችና ወላጆች መካከል ትብብርና መግባባት ይጠይቃል። ይህ የወላጅ ቼክሊስት** (**የመቆጣጠርያ ዝርዝር**) **ልጅዎን መልካም የማጥናት ልምዶች እንዲያዳብር እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ እና የቤት ስራዎቻቸውን በስኬታማነት እንደሚፈፅም የተወሰኑ ጠቃሚ ጥቆማዎች ይሰጣል።**

- ✓ **ትምህርትና የቤት ስራዎች አስፈላጊነታቸውን እንደሚያምኑባቸው ያሳዩ።** **ይህንንም፣ ለቤት ስራ መደበኛ ግዜ በማስቀመጥ፣ ከልጅዎ ጋር ሆነው ግቦችን በማስቀመጥ፣ ፀጥታማ ቦታ በመምረጥ፣ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ መገልገያዎችን በማቅረብ ሊያሳዩ ይችላሉ።**

- ✓ **አመራር መስጠት** ስራውን እርስዎ ራስዎ ሳይሰሩ አመራር ሊሰጡ ይችላሉ!  ልጅዎ ራሱን/ራሷን እንዲያደራጅ/እንድታደራጅ ያግዙ እናም ለወደፊት የሚመጡትን ስራዎቻቸውም ክትትል ያድርጉ፣ ስራዎቻቸውን ለመፈፀም ያላቸውን ግዜ እንዴት እንደሚያስተዳድሩ ያስተምሯቸው፣ የልምምድ ፈተናዎች ይስጧቸው እናም ለትንሹም ለትልቁም ግኝቶቻቸው ያመስግኗቸው።

- ✓ **MCPS ለሁሉም ተማሪዎች የሚያቀርባቸውን ነፃ የቤት ስራ መገልገያዎች እንዲጠቀሙባቸው አበረታቷቸው።**የመገልገያዎቹን ዝርዝሮችና ምን እንደሚያቀርቡ ገለፃዎች [እዚህ ](#)ሊያገኙ ይችላሉ።

- ✓ **ፕሮብሌሞችን ለመፍታትና እንቅፋቶችን ለመወጣት ከልጅዎ አስተማሪ ጋር አብረው ይስሩ።** ከአስተማሪዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ወሳኝ ነው። ከያንዳንዳቸው የልጅዎ አስተማሪዎች ጋር ችግሮች ከመከስታቸው በፊት በአመቱ መጀመርያ ላይ ይነጋገሩ። ስለ ልጅዎ ግስጋሴ ቀጣይ መረጃ እንዲኖርዎ በመምህር-ወላጅ ስብሰባዎችና በትም/ቤቱ በአል ላይ መገኘትዎን ያረጋግጡ። በቤት ስራም ሆነ በትም/ቤት ባጠቃላይ ልጅዎ ችግር እንዳለው የሚጠረጥሩ ከሆነ፣ ከአስተማሪው/ዋ ጋር ችግሩን መፍቻ ፕላን ለመቀየስ ቀጠሮ ይጠይቁ።

- ✓

[የቤት ስራ መገልገያዎች](#)

የወላጅ መመርያዎች ስለ ስርአተ ትምህርት

[ስርአተ ትምህርት 2.0](#)፣ ለኤሌሜንታሪ መማርያ ክፍሎች የተሻሻለው ስርአተ ትምህርት፣ ከሙአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል በሁሉም ትም/ቤቶች በዚህ አመት ተግባራዊ ሆኗል።  ከዚህም የማስመረቂያ ሂደት አካሎች አንዱ፣ MCPS የወላጆችን ስርአተ ትምህርት መመርያ ለኤሌሜንታሪ መማርያ ክፍሎች፣ እንደገና መቀየሱ ነው። እነዚህ መመርያዎች ወላጆችን ስለየክፍሉ ደረጃ ፕሮግራም አጠቃላይ መግለጫ ይሰጧቸዋል እናም ልጅዎ በስነጥበብ፣ ሂሳብ፣ ሙዚቃ፣ የአካል ማጠንከርያ፣ ንባብ/ቋንቋ ስነጥበባት፣ ሳይንስ፣ እና ማህበራዊ ጥናቶች ምን እንደሚማር/እንደምትማር ያስረዳል። በመመርያው ውስጥ፣ አስተሳሰብንና የአካዴሚያዊ ስኬት ችሎታዎች ለያንዳንዱ ማርክ መስጫ ወቅት ትኩረት የሚሰጥባቸው ፅንሰሀሳቦችና ርእሶችን ጨምሮ የሚያብራሩ መረጃዎች ያገኛሉ። በነዚህ መመርያዎች የሚገኙ መረጃዎች በትምህርት አመት በሞላ ለልጅዎ ድጋፍ በመስጠት ረገድ ያግዙዎታል። ከሙአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ተማሪዎች ያሏቸው ወላጆች መመርያውን ከልጃቸው ትም/ቤት መቀበል አለባቸው። እነዚህ መመርያዎች [በኢንተርኔት መስመር ላይ በAdobe Acrobat PDF ቅርፀት](#) ይገኛሉ።

[የኤሌሜንታሪ ትምህርትና ክንውን](#)

[ስርአተ ትምህርት 2.0](#)

**የትምህርት ቤት** Open Houses **በአል ለኦክቶበር** 14 **እንዲከበር ተወስኗል**

**ቀኑን ያስታውሱ!** MCPS **ሰኞ ኦክቶበር** 14**ን ትምህርት ቤቶች ኦፐን ሃውዝስ በአል እንዲያከብሩበት ሰይሞታል። ልጆቻቸውን በመማርያ ክፍል ውስጥ ለመታዘብ፣ ስለትም/ቤቱ ፕሮግራሞች ለመማርና የትም/ቤቱን መምህራኖችና ሰራተኞች ለማግኘት፣ ለወላጆች ትልቅ እድል ነው። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ትም/ቤት ያጣሩ።**

**የፋይናንሳዊ እርዳታዎች አውደጥናት ለ**2**ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ተዘጋጅቷል**

**ስለኮሌጅና እንዴት እንደሚከፈልበት እያሰቡበት ከሆነ፣ በፎል ወራት የተለያዩ የ**MCPS 2**ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች በሚካሄደው [ነፃ የፋይናንሳዊ እርዳታዎች አውደጥናት] ወቅት ይበልጥ ይማሩ። ወላጆችና ተማሪዎች ፋይናንሳዊ እርዳታ ምን እንደሆነ፣ ምን ምን አይነት የፋይናንስ እርዳታዎች እንዳሉና ተማሪዎችስ እንዴት አድርገው ፍላጎትን መሰረት ባደረጉ የፋይናንስ እርዳታ ማመልከት እንዳሚችሉ፣ በነዚህ አውደ ጥናቶች ይማራሉ። የመጀመርያው አውደ ጥናት የተመደበው ለማክሰኞ ኦክቶበር** 8 **በስፐሪንግብሩክ** 2**ኛ ደረጃ ትም/ቤት ነው።**

[**የፋይናንስ እርዳታ አውደ ጥናቶች**]

**በ**Montgomery County **አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን ይሳተፉ!**

**የ**Montgomery County 27**ኛው አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን ለቅዳሜ ኦክቶበር** 26 **እንዲውል ተወስኗል። የ**MCPS **ተማሪዎች ከነሱ** PTA **ወይም ከማህበረሰብ በጎአድራጎት ጋር የአገልግሎት ፕሮጀክት በመተለም እንዲሳተፉ እናበረታታለን። ፕሮጀክቶቹ ከኦክቶበር** 21 **እስከ** 27 **ባለው ሳምንት በማንኛውም ወቅት ሊከናወኑ ይችላሉ። ተማሪዎች በትም/ቤት የፅዳት ወይም የመሬት ማሳመርያ ፕሮጀክት ፕላን ማድረግ ይችላሉ፣ አገልግሎት መማርያ ትርእይት፣ ለቤትየለሾች አነስተኛ የግር ጉዞ (ገንዘብ መሰብሰብያ) ወይም ሌላ ስሜታቸውን የሚቀስቅስ ፕሮጀክት። ይህ ለወላጆችም ሆነ ለተማሪዎች አንድ ላይ ለማገልገል መልካም አጋጣሚ ነው። ተማሪዎች ፕሮጀክቶቻቸውን ወደ**[Community Service Day (**የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን) ድር ጣብያ**] **መጨመር ወይም የነፃ አገልግሎት ለመስጠት መፈረም ይችላሉ። ተማሪዎች ለዚህ ስራ** Student Service Learning (SSL) **(የተማሪ አገልግሎት ትምህርት) ሰአቶች ማግኘት ይችላሉ።**

[**የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን**]